# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# "የፌደራል ፍርድ ቤቶች ረቂቅ አዋጅ "

**ታህሳስ 2012 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**አዋጅ ቁጥር _______/ 2012**

**<u>የ2012 ዓ.ም. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች(ረቂቅ) አዋጅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት የዳኝነት ሥልጣን በፌዴራል እና በክልሎች ፍርድ ቤቶች በመሆኑ፤

ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት የማቅረብና ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለዉ መሆኑ፤በህገ መንግስቱ የተደነገገ በመሆኑ፤

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ለሕግ የበላይነት፣ ለሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የበኩላቸውን የማይተካ ሚና የሚወጡበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ ስለዳኝነት ነፃነት በተደነገገዉ መሠረት ተግባራቸውን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ውጤታማ ፣ ቀልጣፋ ፣ ተደራሽ እና ተገማች የሆነ አገልግሎት መስጠታቸው አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዳኝነት ሥርዓቱን ለማጠናከር የፌደራል ፍርድ ቤቶች በበጀት ምደባና አስተዳደር፣በሰው ሀብት ቅጥርና ምደባ እንዲሁም አስተዳደር ራሳቸውን ችለው የሚሰሩበትን የሕግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 በተደጋጋሚ መሻሻሉ ለአሰራር አመቺ ባለመሆኑና በተሻሻለ አዋጅ መተካት ስላስፈለገ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጃል፡፡

**<u>ምዕራፍ አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ አዋጅ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር —— / 2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ:

   1) "ሕገ መንግስት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ነው፡፡
   2) "የፌዴራል መንግሥት ሕጎች" ማለት በፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን ክልል ሥር የሚወድቁ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን ይጨምራል፤

3) “ፌዴራል ፍርድ ቤቶች” ማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ናቸው፤

4) “መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት” ማለት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት ያለበትን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሰረት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊታይ የሚችልን የመጨረሻ ዉሳኔ፣ ፍርድ፣ ብይን፣ትእዛዝ፣ ያጠቃልላል።

(ሀ) የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን

(ለ) ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ሕግ የሚጠቅስ

(ሐ) ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፤

(መ) በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፤

(ሠ) በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፤

(ረ) ጉዳዮን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖር የተወሰነ ፤

(ሰ) የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠው ውሳኔ

(ሸ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ፡

5) “የመጨረሻ ውሳኔ” ማለት በፍርድ ቤት ፣ በሕግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል፣ በተቋማት ወይም በአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች የተሰጠ እና ለጉዳዩ እልባት የሚሰጥ ፍርድ ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ፣ ውሳኔ እና/ወይም የይግባኝ ሂደቶችን የጨረሰ ፍርድ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔን ይጨምራል።

6) «የፌደራል መንግስት ባለስልጣኖች» ማለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌደሬሽን ምክር ቤት አባላት፣ ከሚኒስቴር ደረጃ በላይ የሆኑ የፌደራል መንግስቱ ባለስልጣኖች፣ሚኒስትሮች እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የፌደራል መንግስት ባለስልጣኖች ናቸዉ።

7) «የፌደራል መንግስት ሰራተኞች» ማለት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 ስር ከተጠቀሱት ዉጭ ያሉ በፌደራል መንግስት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ያጠቃልላል።

8) **"የአስተዳደር ሠራተኛ"** ማለት ከዳኛ እና ከተሿሚ የአስተዳደር ሰራተኛ ዉጭ ያለ ሁሉንም የፍርድ ቤት ሰራተኛ ያጠቃልላል።

9) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠዉ/ጣት ሰዉ ነዉ/ናት።

## ምእራፍ ሁለት

## ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን

**3. መሠረቱ**

**1)** የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል ፡

ሀ) ሕገ መንግሥቱን፣ የፌዴራል መንግሥቱን ሕጎች ወይም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸዉ እና ያፀደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ በሚነሱ ጉዳዮች

ለ) በፌዴራል መንግሥቱ ሕግ ተገልጸው በተወሰኑ ባለጉዳዮች፤

ሐ) በሕገ መንግሥቱ ወይም በፌዴራል መንግስት ሕግ በተገለጹ በታዎች፡

2) የፌደራል ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 9(2) እና 13(1) መሰረት የህገ መንግስቱን ድንጋጌወች ተግባራዊ ያደርጋሉ።

**4. የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን**

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

1) በአገር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣

2) በውጭ ሀገር መንግሥት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

3) ዓለም አቀፍ ሕጐችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤

4)ከአንድ ክልል በላይ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ አገልግሎት በሚሰጡ መገናኛዎች ደህንነትና ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

5)የበረራ ደህንነትን የሚመለከቱ ወንጀሎች፤

6) ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ሕጎችና ልምዶች እንዲሁም ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የውጭ ሀገር አምባሳደሮች፣ ቆንስሎች፣ የዓለምአቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ መንግሥታት ወኪሎች ተጠያቂ በሚሆኑባቸው ወይም ልዩ መብትና ጥበቃ ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ሰዎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፣

7) የአደገኛና አደንዛዥ ዕጾች ሕገ-ወጥ ዝውውርን የሚመለከቱ ወንጀሎች፣

8) በተለያዩ ክልሎች ወይም በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልል ሥር በሚወድቁና በተያያዙ ወንጀሎች፣

9) በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ጎሣዎች፣ በሀይማኖት ተከታዮች ወይም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ከተፈጠረ ግጭት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፣

10) በፌዴራል መንግሥቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤

11) በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤

12) በታዎቁ ገንዘቦች፣የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ቴምብሮች ወይም መሳሪያዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤

13) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) እና አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከ5 ዓመት ጽኑ እሥራት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ የውጭ ሀገር ዜጎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፣
14) የፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣኖች በማናቸዉም የወንጀል ጉዳዮች እና የፌደራል መንግስት ሠራተኞች በሥራቸው ወይም በኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ የሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች
15) በፌዴራል መንግሥቱ ንብረቶች ላይ በሚፈጸሙ እና የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) እና አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከ5 ዓመት ጽኑ እሥራት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎች
16) በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ በሚነሱ ማናቸዉም የወንጀል ጉዳዮች እና
17) በሌሎች ሕጐች በተጠቀሱ ጉዳዮች።

## 5. <u>የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን</u>

1) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል ፡

ሀ) የግለሰብ  ዓለም አቀፍ ሕግን በሚመለከቱ ጉዳዮች፤

ለ) የውጭ ሀገርን ፍርድ ወይም ብይን ለማስፈፀም በሚቀርብ አቤቱታ፤

ሐ) ዜግነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ ክርክሮች፣

መ) ከመክሰር ጋር በተያያዙ ጉዳዮች

ሠ) ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ሕጐችና ልምዶች እንዲሁም ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የውጭ ሀገር አምባሳደሮች፣ ቆንስላዎች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ መንግሥታት ወኪሎች ተጠያቂ በሆኑባቸው ወይም/እና ልዩ መብትና ጥበቃ ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ሰዎች ተከራካሪ በሆነበት ጉዳዮች፣

ረ) የፌዴራል መንግሥት አካል ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ

ሰ) የፌዴራል መንግሥቱን ንብረቶች የተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፤

ሸ) መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች፣ በክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ፣ በክልል እና በድሬዳዋ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ጉዳዮች፣

ቀ) የፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች በስራቸዉ ወይም በሃላፊነታቸዉ ምክንያት ኃላፊ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች፣

በ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (2) እና አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የውጭ አገር ዜጋ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የሆነበት ጉዳይ፤

ተ) በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች፣

ቸ) የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች ፤

አ) በፈጠራ፣ በድርሰትና ሥነ ጥበብ፣ ቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ባለቤትነት በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች፣

ነ) የኢንሹራንስ ውልን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች፣

ኘ) ተገዶ የመያዝ ሕጋዊነትን ለማጣራት የሚቀርብ
አቤቱታ

ደ) በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች የሚነሱ የፍታብሄር ጉዳዮች እና

ጀ) በሌሎች ሕጐች የተጠቀሱ ጉዳዮች።

2) የክልል ጉዳይ በክልሉ ፍርድ ቤት እየታየ እያለ ወይም ከተወሰነ በኋላ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 «ሸ» እና «ነ» ላይ የተጠቀሰ ተከራካሪ በማንኛውም ሁኔታ ወደ ክርክሩ ቢገባ እንኳ ጉዳዮ በክልሉ ፍርድ ቤት መታየቱ ይቀጥላል።

## 6. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው መሠረታዊ ሕጎች

1. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልላቸውን መሠረት አድርገው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ወይም ክርክሮችን ቀጥሎ የተጠቀሰውን መሠረት አድርገው ይዳኛሉ

ሀ) ህገ መንግሥቱን ፣ የፌዴራል መንግሥቱን ሕጐችና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸዉን ዓለም አቀፍ

ስምምነቶች

ለ) ጉዳዩ የክልል ፣የአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተሞችን ሕግ የሚመለከት

ሆኖ ሲገኝ የክልሉን ወይም የከተማውን ሕግ ።

## 7. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው የሥነ ሥርዓት ሕጎች

በሥራ ላይ ያሉ የወንጀል እና የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

## ምእራፍ ሦስት

## ስለ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

## 8. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን፤

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

1) በሕግ በሚወሰነው መሠረት አንድ ጉዳይ ከአንድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት ወደ ሌላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት ወይም በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጡ የፌዴራል

ጉዳዮችን በሚመለከት ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲዛወር በሚቀርብ ጥያቄ እና

2) በሌሎች ህጎች በተጠቀሱ ጉዳዮች።

**9. <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን</u>**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚከተሉትን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፤

1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሣኔ የሰጠባቸው፣
2) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠባቸው ፣
3) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጉዳዩችን በተወካይነቱ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ የሰጠባቸው፣
4) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጉዳዮችን በተወካይነቱ በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠባቸው፣
5) በሌሎች ሕጐች የተጠቀሱ ጉዳዮችን።

**10.<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣን</u>**

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ያለባቸውን የሚከተሉትን ጉዳዮች በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

ሀ) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ፤

ለ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸው፤

ሐ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (4)(ሀ) እና (ሸ) ን በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው፣

መ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (4)(ለ) በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው እና ጉዳዮቹ ሰፋ ያለ ህብረተሰብ ክፍል መብቶችን ሊመለከቱ የሚችል ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ሲሆኑ

ሠ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም የየክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ በተሰጣቸዉ የዉክልና ስልጣን የፌደራል ጉዳይን አይተዉ የመጨረሻ ዉሳኔ የሰጡበት፤

ረ) የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ፤

ሰ) በሕግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በሌሎች አካላት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ፤

ሸ) አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ፤ በፌዴራል ፍርድ ቤት ሊታይ ይችል በነበረ ጉዳይ ላይ በአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች መሠረት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ፤

ቀ) በሌሎች ሕጐች የተጠቀሱ ጉዳዮች።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(መ) እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (4)(ሀ) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ጋር ተያይዞ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ፣ በማህበራዊ ፍርድ ቤት በተጀመሩ አነስተኛ ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ የመጨረሻ ውሳኔ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚጠቀሱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ በሚሰጥ የመጨረሻ ዉሳኔ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አይቀርብም።
3) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየትኛዉም ደረጃ በሚገኝ የፌደራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤት አስገዳጅነት ይኖረዋል።
4) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎቶች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በኤሌክትሮኒክስ ወይም በህትመት ሚዲያዎች በተቻለ ፍጥነት ያሰራጫል።

## ምእራፍ አራት
## ስለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

### 11.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን

1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምታቸዉ ከአስር ሚሊዮን (10,000,000 birr) በላይ በሆኑ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

ሀ) የዚህ አዋጅ በአንቀጽ 14 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 5 መሰረት በሚነሱ ማናቸዉም የፍታብሄር ጉዳዮች።
ለ) በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ በሚነሱ ማናቸዉም የፍታብሄር ጉዳዮች።

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1)(ሀ) ቢኖርም፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፤

(ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) እስከ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሠ) ላይ በተጠቀሱት የፍትሐብሔርጉዳዮች፤

(ለ) በሕግ በሚወሰነው መሠረት አንድን ጉዳይ ከአንድ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት ወደ ሌላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር የሚቀርብን ጥያቄ፤

(ሐ) በሌሎችህጐችየተጠቀሱጉዳዮች፡፡

3) በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንዲሁም በሌሎች ህጎች የተመለከተዉ ቢኖርም የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ ታይተዉ ሊዎሰኑ የሚችሉ በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት ስር የተመለከቱ መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶችን ለማስከበር ለጉዳዩ ተገቢ የሆነ ፍርድ፣ትዕዛዝ ወይም ዉሳኔ የመስጠት ስልጣን አለዉ፡፡
4) ማንኛዉም በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ ሰዉ ወይም ጉዳዩን ለማቅረብ በቂ ምክንያት ያለዉ ሰዉ መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶችን ለማስከበር ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ መብት አለዉ፡፡
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የተጠቀሰዉ ጉዳይ የሚስተናገደዉ የፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ስለ አጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ላይ ስለሚፈጸሙ ስነ-ስርዓት በሚል በተደነገገዉ መሰረት ይሆናል፡፡

## 12.<u>ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፣

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 4 ላይ የተመለከቱና አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡ በፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፤
2) በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ በሚነሱና አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚቀርቡ በሌሎች የወንጀል ጉዳዮች እና
3) በሌሎች ሕጐች ለፌዴራል ፍርድ ቤት በተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፡፡

## 13.<u>የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ዳኝነት ሥልጣን</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚከተሉትን የፍትሐብሔር እና የወንጀል ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡

1) የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እና
2) በሌሎች ሕጐች የተጠቀሱ ጉዳዮችን፡፡

## 14.<u>የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐ ብሔር ዳኝነት ሥልጣን</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 እና 11 ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 5 መሠረት በሚቀርቡ የፌዴራል የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች፤
2) በሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በሚነሱ ሌሎች የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች፣ እና
3) በሌሎች ሕጐች የተጠቀሱ የፍታብሄር ጉዳዮች፡፡

## 15.የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወንጀል የመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 4 ላይ የተመለከቱና አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የማይቀርቡ በፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች
2) በሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ በሚነሱ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማይታዩ ሌሎች የወንጀል ጉዳዮች እና

3)በሌሎች ሕጐች የተጠቀሱ ጉዳዮች።

## 16. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አግባብነት ባላቸዉ ህጎች በግልጽ በተሰጡት ጉዳዮች ላይ በይግባኝ የማየት ስልጣን ይኖረዋል።

## ምእራፍ አምስት

## ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች ኘሬዚዳንቶች፣ ም/ኘሬዝዳንቶች፣የምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኞች እና ሰብሳቢ ዳኞች

## 17. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት በሕግ መሠረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ለማስተዳደር ኃላፊ ይሆናል/ትሆናለች።
1) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል/ይኖሯታል፡

ሀ) ለፌዴራል ዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞችን፣ የምድብ ችሎቶች ተጠሪ ዳኞችን እና ሰብሳቢ ዳኞችን መደልደል፣ ሥራ መስጠት፣

ለ) ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን መቅጠር፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2)(ሠ) ላይ የተጠቀሰውን ጨምሮ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ/ታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ማዋል፣

መ) በዚህ አዋጅ ላይ በተጠቀሰው መሠረት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መውጣት ያለባቸው ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲዘጋጁና እንዲወጡ በማድረግ ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

ሠ) የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን በውክልና ለሚሰሩ የክልል ፍርድ ቤቶች የበጀት ማካካሻ ጥያቄ ላይ ውሳኔ መስጠት፤

ረ) የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን አስመልክቶ በውክልና ስላከናወኑት ተግባር በስታስቲክስ የተደገፈ ሪፖርት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ማድረግ፣

ሰ) የዳኞችና የሌሎች ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና የሚካሄድበትን ሁኔታ እንደአስፈላጊነቱ ማመቻቸት፣

ሸ) በክልል ስለሚታዩ የፌዴራል ጉዳዮች የመዝገብ አያያዝና ጠቅላላ አሠራር ከክልል ፍርድ ቤቶች ጋር መመካከር የሚሻሻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

ቀ) ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የበጀት አፈጻጸም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣

በ) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ተቋም ፣ የተከላካይ ጠበቆችን ቢሮ እና በሕግ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ተግባራትን ለማስፈፀም የሚያስችሉ የሥራ ክፍሎች እንዲደራጅ ማድረግ፤

ተ) የፌዴራል ፍ/ቤቶች ዳኞች ስልጠና መመሪያ ማዉጣት።

ቸ) ለኢትዮጵያ የዳኝነት ሥርዓት እድገት፤ ቀልጣፋ አሰራር እና ውጤታማነት የሚያግዙ ጥናቶች እንዲደረጉ ማድረግ፤ ተግባራዊነታቸው መከታተል፤

ነ) እንደአስፈላጊነቱ የፌዴራል ሸሪአ ፍርድ ቤቶች በተቋቋሙበት አዋጅ መሠረት የዳኝነት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ድጋፍ መስጠት

ኘ) በሕግ እና በዚህ አዋጅ የተሰጡ ሌሎች ተግባሮች ማከናዎን።

**18. <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ኘሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ኘሬዚዳንት የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባር ይኖሩታል/ሯታል።

1) በኘሬዝዳንት የሚመራለትን/ላትን ሥራ ማከናዎን፣
2) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት በማይኖርበት/ትኖርበት ጊዜ ኘሬዚዳንቱን/ቷን ተክቶ መስራት፤

**19. <u>ስለ ፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንትና ምክትል ኘሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር</u>**

1) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የመምራት እና ክትትል የማድረግ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የየፍርድ ቤቱ ኘሬዚዳንቶች፣

ሀ) ፍርድ ቤቱን ይወክላሉ

ለ) የፍርድ ቤቱን ዳኞች ይደለድላሉ፣ ሥራ ይሰጣሉ፣ ያስተዳድራሉ፣

ለ) የፍርድ ቤቱን ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ያስተዳድራሉ፣

ሐ) የየፍርድ ቤቱን ፋይናንስ ያስተዳድራሉ

መ) በሕግ እና በዚህ አዋጅ የተሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ።

2) የፍርድ ቤቱን ዕቅድና በጀት አዘጋጅተው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ያቀርባሉ ፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላሉ፣
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የታቀዱ ስራዎች ቀልጣፋ እና ዉጤታማ በሆነ መንገድ እንዲከናዎኑ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚዘረጋዉ የተጠያቂነት ስርዓት የሚመዘን ይሆናል።
4) ስለ ፍርድ ቤቱ ሥራ እንቅስቃሴ በየጊዜው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባሉ፣
5) የፌዴራል የከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የየራሳቸው ምክትል ኘሬዚዳንቶች ይኖሯቸዋል።
6) የየፍርድ ቤቱ ምክትል ኘሬዚዳንቶች የፍርድ ቤቱ ኘሬዚዳንት በማይኖሩበት ጊዜ በመተካት ይሰራሉ፤ እንዲሁም በኘሬዚዳንቱ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎች ያከናውናሉ።
7) የፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ኘሬዝዳንቶች እና ምክትል ኘሬዝዳንቶች በፍርድ ቤቶቻቸው በሚገኙ ማናቸዉም ችሎቶች ሰብሳቢ ዳኛ ሆነው ሊያስችሉ ይችላሉ።

**20. <u>ስለ ምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኛ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1) የፌዴራል ከፍተኛ እና መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤቶች በሚያስችሉበት ምድብ ችሎቶች የየራሳቸዉ ተጠሪ ዳኛ ይኖራቸዋል።
2) የየምድብ ችሎቶቹ ተጠሪ ዳኞች ከዳኝነት ሥራ በተጨማሪ ከየፍርድ ቤቶች ኘሬዝዳንቶች በሚሰጧቸዉ የስራ መመሪያ መሰረት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናዉናሉ።

ሀ) የምድብ ችሎቶቹን ሥራ ማስተባበር፤

ለ) ለሚቀርቡ አስተደደራዊ ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት፣ ሠራተኞችን ማስተዳደር፤

ሐ) በምድብ ችሎቶቹ ስለተከናወኑ ሥራዎች ለየፍርድ ቤታቸው ኘሬዝዳንት ሪፓርት ማቅረብ፣

መ) የየፍርድ ቤቱ ኘሬዝዳንት የሚሰጧቸዉን ሌሎች ተግባራት ማከናዎን።

3) የፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት በሚሰጣቸዉ ዉክልና መሰረት የምድብ ችሎቱን ፋይናንስ ማስተዳደር።

**21. <u>ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤት የችሎት ሰብሳቢ ዳኛ</u>**

ሶስትና ከሶስት በላይ የሆኑ ዳኞች በሚያስችሉበት የፌዴራል ፍርድ ቤት ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ይኖረዋል።

**22. <u>የፌዴራል ፍርድ ቤት ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ተግባር</u>**

1) የፌዴራል ፍርድ ቤት ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናዉናል/ታከናዉናለች

ሀ) የችሎቱ ሥራ በህግ መሠረት መመራቱን በማረጋገጥ ችሎቱን ማስተዳደር

ለ) በችሎቱ የሚወሰኑ መዝገቦች በሁሉም የችሎቱ ዳኞች ግንዛቤ የተወሰደባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ) ለችሎቱ የተመደቡ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችን ማስተዳደር

መ) ሁሉም የችሎቱ ዳኞች በችሎቱ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በማዘጋጀት ተመጣጣኝ ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተል።

2) ሰብሳቢ ዳኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ተግባራት የችሎቱን ዳኞች የዳኝነት ነፃነት በማይጋፋ ሁኔታ ይፈጽማል/ትፈጽማለች።

**<u>ምእራፍ ስድስት</u>**

**<u>ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራ አካሄድ</u>**

**23. <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ሌሎች ባለሙያዎች እና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች</u>**

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ኘሬዚዳንት፣ አንድ ምክትል ኘሬዝዳንት እንዲሁም የዳኝነት ስራዉን ለማከናዎን አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል።

2) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚያስተዳድራቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳይሬክተሮች፣ ሬጅስትራሮች፣ የዳኛ ረዳቶች ፣ የህግ ባለሙያዎች እና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል።

**24. <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች</u>**

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የፍታብሄር እና የወንጀል የመጀመሪያ ደረጃ፣ ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ይኖሩታል።

2) በእያንዳንዱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከ3 (ሶስት) ባላነሱ ዳኞች የሚያስችሉ ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ደግሞ ከ 5 (አምስት) ባላነሱ ዳኞች ያስችላሉ።

3) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንት እና ምክትል ኘሬዝዳንት በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚገኙ ማንኛዉም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ሆነው ሊያስችሉ ይችላሉ።

**25. <u>ከሰባት ያላነሱ ዳኞች ስለሚሰየሙበት የሰበር ችሎት</u>**

1) አምስት ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት በባለጉዳዮቹ አመልካችነት ወይም በችሎቱ በራሱ አነሳሽነት ቀድሞ የተሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በተለያዩ ምክንያቶች ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘዉ ከሰባት ባላነሱ ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት እንዲታይ በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶችን ተንትኖ በመግለጽ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ማቅረብ ይችላል።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተገለጸዉ መሰረት ጥያቄ ሲቀርብለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች የሚሰየሙበት የሰበር ችሎት ጉዳዩን እንዲታይ ያደርጋል።

3) በዚህ አንቀጽ የተገለጸዉ የሰበር ችሎት የሚሰጠዉ የህግ ትርጉም ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በማንኛዉም ደረጃ ለሚገኝ ፍርድ ቤት አስገዳጅ ይሆናል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ መሰረት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት ቀድሞ የሰጠዉን የህግ ትርጉም ከሰባት ባላነሱ ዳኞች በተመሳሳይ ጭብጥ በሌላ ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

**26. <u>የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት</u>**

1) ለሰበር ችሎት የሚቀርብ የሰበር ማመልከቻ በውሳኔው ላይ የተፈፀመውን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (4) ላይ ከተሰጠው ትርጉም አንፃር ተገናዝቦና የሚጠየቀውን ዳኝነት በሚገልፅ መልኩ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን በተመለከተ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በአጭሩ ተፅፎ መቅረብ አለበት፡፡
2) የሚመለከተው አቤት ባይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው መሠረት ከሚያቀርበው ማመልከቻው በተጨማሪ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ እና የበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅጂዎችን ማቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም የሰበር ችሎቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በስር ፍርድ ቤት ያለዉ ሙሉ መዝገብ ቅጅ እንዲቀርብለት ያደረጋል፡፡
3) የሰበር ጥያቄ ማመልከቻ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት 90 (በዘጠና) ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

**27. <u>የሰበር አቤቱታን በሰበር ሰሚ ችሎት ስለማየት</u>**

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሰበር ችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ክርክር አመራር ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ የሚያወጣው ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት አቤቱታ በሰበር የሚሰማው አስቀድሞ ሶስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት ውሳኔው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (4) እና አንቀጽ 10 ላይ በተመለከቱት መሠረት ለሰበር ችሎት መታየት አለበት ብሎ ሲወሰን ነው፡፡
2) የሰበር ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የተመራለትን ጉዳይ መርምሮ አቤቱታ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለመኖሩን ከተረዳ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
3) የሰበር ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የተመራለትን ጉዳይ መርምሮ አቤቱታ በቀረበበት ጉዳይ ላይ ያስቀርባል ብሎ ከተረዳ ጭብጥ በመያዝ በተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በአመልካች ከቀረበው የሰበር ማመልከቻ እና መጥሪያ ጋር ይልካል፡፡
4) ተከራካሪዎች መልስ እና የመልስ መልስ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበው ከተቀባበሉ በኋላ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ተከራካሪዎችን መስማት ካላስፈለገው በስተቀር በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**28. <u>የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ዳኞች፣ ችሎቶችና ሌሎች ሠራተኞች</u>**

1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞችና ችሎቶች ይኖሯቸዋል፡፡

2) የፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) እና አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የየፍርድ ቤቱ ኘሬዝዳንቶች የሚያስተዳድሯቸው ሬጅስትራሮች ፣ የዳኞች ረዳቶች ፣ የህግ ባለሙያዎች እና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሯቸዋል።
3) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎቶች በአንድ ዳኛ ያስችላሉ።
4) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 እንደተጠበቀ ሆኖ

ሀ) ከ15 አመት በላይ የሚያስቀጡ የወንጀል ጉዳዮች በሶስት ዳኞች ይታያሉ

ለ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ የተወሰኑ ጉዳዮች በፌዴራል ከፍተኛ እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በሶስት ዳኞች እንዲታይ ሊደረግ ይችላል።

**29. <u>ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ሥፍራ</u>**

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማስቻያ ሥፍራ አዲስ አበባ ይሆናል።
2) የፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ስፍራ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በድሬዳዋ ከተማ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 322/95 በተመለከቱት ክልሎች መሠረት እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ (2) ወደፊት ሊወሰኑ በሚችሉ ቦታዎች ይሆናል።
3) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ቦታዎች የፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችን ያደራጃል።

**30. <u>የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ</u>**

1) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል።

2) የአማርኛ ቋንቋ ለማይችል ሰው ፍርድ ቤቱ ብቃት ያለው አስተርጓሚ ይመድብለታል፡

3) የምልክት ቋንቋ ለሚጠቀም አካል ጉዳተኛ በተመሣሣይ የምልክት ቋንቋ ችሎታ ያለዉ ባለሙያ ይመደብለታል።

4) በየደረጃዉ ያሉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የተሟላ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የአስተርጓሚ ቢሮ ያደራጃሉ።

**31. <u>በግልጽ ችሎት ስለማስቻል</u>**

1) ፍርድ ቤቶች ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያስችላሉ።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም

ሀ) የተከራካሪዎቹን የግል ህይዎት፣

ለ) የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ፣

ሐ) የሕዝብ ሞራል ሁኔታ ወይም ግብረገብነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች በዝግ ችሎት ያስችላሉ።

**32. <u>የዳኞች ከችሎት መነሳት</u>**

1) የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኛ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ከችሎት ይነሳል/ትነሳለች።

ሀ) ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛዉ/ዋ ወገን ወይም ከጠበቃዉ/ዋ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው/ያላት እንደሆነ፣

ለ) ከተከራካሪዎቹ የአንደኛዉ/ዋ ወገን ሞግዚት፣ ነገረ ፈጅ ወይም ጠበቃ በሆኑበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር እንደሆነ፣

ሐ) ክርክር የተነሣበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት፣ በግልግል ዳኝነት፣ በዕርቅ ያየዉ/ያየችዉ ሆኖ ከተገኘ። ሆኖም አግባብ ባለዉ የስነ ስርዓት ህግ መሰረት የይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ቀድሞ ወደወሰነዉ ፍርድ ቤት በመመለስ ሂደት ጉዳዩ የተመራለት ዳኛ ላይ ይህ ተፈጻሚ አይሆንም።

መ) ከተከራካሪዎቹ ወገኖች ከአንደኛዉ/ዋ ወይም ከጠበቃዉ/ዋ ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለዉ/ያላት እንደሆነ፤

ሠ) ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እስከ (1)(መ) ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጭ ትክክለኛ ፍትሕ አይሰጥም/አትሰጥም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዳኛው/ዋ በችሎት ላይ ሊቀመጥ/ልትቀመጥ የማይገባዉ/ት መሆኑን ሲያዉቅ/ስታዉቅ ከችሎት ተነስቶ/ታ ሌላ ዳኛ መተካት አለበት/ባት፡

**33. <u>ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ/እንድትነሳ ስለማመልከት</u>**

1) ከተከራካሪዎች አንደኛው/ዋ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 31 በተዘረዘሩት ምክንያቶች ዳኛ ከችሎት መነሳት ያለበት/ባት እንደሆነ ይህንኑ በሚመለከት ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች፡
2) ማመልከቻው የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ/ቿ እንዳወቀ/ች ወዲያውኑ መሆን አለበት።
3) ዳኛው/ዋ ብቻቸውን/ዋን የሚያስችል/የምታስችል ከሆነ እና ከችሎት ስለመነሳት የሚቀርበውን ማመልከቻ ተመልክቶ/ታ ጥያቄውን የተቀበለ/ች እንደሆነ ከችሎት ይነሳል/ትነሳለች። ጥያቄውን ያልተቀበለ/ች እንደሆነ ግን በዚያው ፍርድ ቤት በሚገኝ ሌላ ችሎት፤ ሌላ ችሎት ከሌለ የዚህኑ ፍርድ ቤት ውሣኔ ይግባኝ በሚያየው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ይተላለፋል።

4) ከችሎት እንዲነሳ/እንድትነሳ ማመልከቻ የቀረበለት/ላት ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር የሚያስችል/የምታስችል ከሆነ ማመልከቻው በዚያው ችሎት ባሉ ሌሎች ዳኞች ይወሰናል።
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚቀርብ ጥያቄ ለአዲሱ ችሎት በደረሰ በ15(አሥራ አምስት) ቀን ውስጥ መወሰን ያለበት ሲሆን የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ይሆናል።
6) የሚሰጠውን ውሣኔ ዳኛው ወዲያውኑ መፈጸም አለባቸው።

**34. <u>ማመልከቻው ስለሚያስከትለው ኪሣራ እና ቅጣት</u>**

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 መሠረት የሚቀርበውን ማመልከቻ ፍርድ ቤቱ ተገቢ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ከቀረ የጉዳዩ ውጤት ከግምት ሳይገባ ኪሣራውን የሚከፍለዉ/ምትከፍለው ማመልከቻውን ያቀረበዉ/ችው ሰው ይሆናል/ትሆናለች።
2) ከተከራካሪዎቹ አንደኛዉ/ዋ ወገን ዳኛው/ዋ ከችሎት እንዲነሳ/እድትነሳ ያቀረበዉ/ችው ማመልከቻ በቂ ምክንያት የሌለዉ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻዉ/ዋን ውድቅ በማድረግ በአመልካቹ/ቿ ላይ ከአንድ ሽህ ብር ያላነሰ ከአምስት ሽህ ብር ያልበለጠ መቀጫ ሊጥል ይችላል።ሆኖም አቤቱታ አቅራቢዉ ሆን ብሎ የዳኛዉን ስም ለማጥፋት ወይም ክብር ለመጉዳት ወይም ጉዳዮችን ለማጓተት ዳኛው ከችሎት እንዲነሳ/እንድትነሳ አቤቱታ ያቀረበ/ች እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከ5,000 ብር ያላነሰ-10,000 ብር ያልበለጠ መቀጫ ሊጥል ይችላል።

## <u>ምእራፍ ሰባት</u>

## <u>ስለፌደራል ፍርድ ቤቶች በጀትና የሰው ሀብት አስተዳደር</u>

**35. <u>የፌደራል ፍ/ቤቶች የበጀት አስተዳደር ነፃነት</u>**

1) የፌዴራል ፍ/ቤቶች ከመንግሥት በጀት ላይ ጥቅል የሆነ የፍርድ ቤት ፈንድ ይመደብላቸዋል።
2) የሚመደበው ጥቅል የሆነ ፈንድ፤ለፌዴራል ፍ/ቤቶች በሕገ-መንግስትና በሌሎች ሕጎች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል መሆን አለበት። ጥቅል በጀቱም የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ. ለዳኞችና ከዳኞች ዉጭ ላሉ ሰራተኞች በቂ ደመዎዝና ጥቅማ ጥቅም ለመክፈል የሚያስችል፤

ለ. አስፈላጊ የሆኑትን የሥራ ማከናወኛ መሳሪያዎችንና አገልግሎቶችን ለመግዛት የሚያስችል፤ እና

ሐ. የካፒታል ዕቃዎችን እና መሰረተ ልማቶችን ለማሟላት የሚያስችል፤

3) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ለሚሰጡት አገልግሎት የሚከፈል የዳኝነት ክፍያ፣ ከቅጣት የሚገኝ ገቢ፣ከለጋሾች የሚገኙ የገንዘብ እና ሌሎች ለፍርድ ቤት የሚከፈሉ ክፍያዎች በፍርድ ቤቶች የተጠቃለለ ፈንድ ዉስጥ ገቢ ይደረጋሉ።

4) በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አማካይነት ለፌዴራል ፍ/ቤቶች የጸደቀ በጀት በበጀት አርዕስት እና ተመሳሳይ መለኪያዎች ሳይወሰን የውስጥ የበጀት ሽግሽግ መብታቸው ተጠበቆ በዕቅድ ላይ በመመሥረት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ጉዳዮች በነፃነት ከሥራ ላይ ያውሉታል፡፡

5) ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚመደበዉ በጀት የፌደራል መንግስቱ አመታዊ በጀት ዉስጥ ከአንድ መቶኛ ያላነሰ መሆን አለበት።

**36. <u>ስለ ፌደራል ፍርድ ቤቶች በጀት</u>**

1) በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 79 (6) በተደነገገው መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት የፌዴራል ፍ/ቤቶችን በጀት አዘጋጅቶ/ታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል/ታቀርባለች፡፡

2) የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ከሌሎች የፍርድ ቤት ኃላፊዎች ጋር በመሆን ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመቅረብ የበጀት ጥያቄውን/ዋን ያስረዳል/ታስረዳለች፡፡

3) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የጸደቀላቸውን በጀት አጠቃቀም አስመልክቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል/ታቀርባለች፡፡

4) የፌዴራል ፍ/ቤቶች የበጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥቱ የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

**37. <u>የፌደራል ፍርድ ቤቶች የስራ ጊዜ</u>**

1) የፌደራል ፍርድ ቤቶች እና ዳኞች የስራ ሰዓት ከሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች የስራ ሰዓት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል።

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ ቢኖርም የፌደራል ፍርድ ቤቶች በየአመቱ ከነሐሴ 1 እስከ መስከረም 30 ድረስ ዝግ ይሆናሉ።

3) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተዉ ቢኖርም በትርፍ ጊዜ በሚሰሩ ዳኞች ፍርድ ቤቶቹ ከስራ ጊዜ ዉጭ አስቸኳይ ጉዳዮችን እንዲያስተናግዱ ሊደረግ ይችላል። ። ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል።

**38. <u>የሰው ሀብት</u>**

1) የፌዴራል ፍ/ቤቶች የእራሳቸውን ከዳኞች ዉጭ ያሉ ሠራተኞችን የመመልመል፣ የመቅጠርና የማስተዳደር ነፃነት አላቸው፡፡

2) ከዳኞች ዉጭ ያሉ ሰራተኞች ምልመላ፣ ቅጥር፣ ምደባ፣ ዕድገት፣ ዝውውር፣ሥልጠና፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ የጥቅማ ጥቅም ክፍያ፣ የሰራተኞች የዲሲፕሊን ጉዳይ እና ተያያዥ ጉዳዮች የሚወሰነው በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተዘጋጅቶ በዳኝነት አስተዳደር ጉባኤው በሚጸድቅ ደንብ አማካይነት ይሆናል፡፡

3) በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚወጣዉ ደንብ የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ. ምልመላ፣ ቅጥር፣ ምደባ፣ ዕድገት፣ ዝውውር፣ሥልጠና፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ የጥቅማ ጥቅም ክፍያ እና የሰራተኞች የዲሲፕሊን ጉዳይ ከማንኛዉም ወገንተኝነት በጸዳ ሁኔታ መከናወን ያለበት መሆን፤

ለ. አዲስሠራተኞችየሚቀጠሩትግልጽ በሆነ ማመልከቻ በዉድድር፣ በፈተና እና በምዘና ሥርዐት ላይ ተመስርቶ ክፍት በታውን አስመልክቶ ከትምህርት፣፣ከብቃት፣ከሙያ፣ከልምድ፣ ከክህሎት፣ልዩ ችሎታ ከመልካም ሥራ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በታው የሚጠይቀውን ልዩ ችሎታን ብቃት አሟልተው መገኘታቸውሲረጋገጥ መሆኑን፤

(ሐ) ከዳኞች ውጭ ላሉ ሠራተኞች የሚፈከል ክፍያ ብቃት ያለቸውን ሠራተኞች ለመሳብና በሥራ ላይ ለማቆየት በቂ መሆኑን እና ክፍያውም መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ልዩ ችሎታ ያላቸውን ሠራተኞችን ለመቅጠርና ለመሳብ በሚያስችል በብቃት ላይ በተመሰረተ ሥርዐት በየጊዜው የሚገመገምና የሚከለስ መሆኑን።

4) የአስተዳደር ሠራተኞች መብትና ጥቅማ ጥቅም በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ለሌሎች የመንግስት ሠራተኞች ከተፈቀደው ያነሰ ሊሆን አይችልም።

**39. <u>ኦዲት</u>**

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሂሳብ መዝገብና የበጀት አጠቃቀም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 መሰረት መከናዎኑን በፌደራል ዋና ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራል።

## <u>ምእራፍ ስምንት</u>

## <u>ስለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉባኤ</u>

**40. <u>የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉባኤ</u>**

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አንድ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ) ይኖራቸዋል።

**41. <u>የጉባዔው አባላት</u>**

1) የጉባዔው አባላት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ኘሬዚዳንቶች፣ ምክትል ኘሬዚዳንቶች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ በፌዴራል ከፍተኛ እና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች የተወከሉ ሁለት ዳኞች ከእያንዳንዳቸዉ አንድ ወንድ አንድ ሴት፤ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ኘሬዚዳንቶች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬድዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች ኘሬዚዳንቶች ይሆናሉ።
2) በጉባዔው ላይ ፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረዉ/ራት ይሳተፋል/ትሳተፋለች።
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ያልተጠቀሱ ዳኞች እና አግባብ ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ ማኅበራትን ፣ ድርጅቶችን ፣ ከፍተኛ የሕግ ትምህርት ተቋማት እና የሳይንስ ተቋሞችን የሚወክሉ ሰዎች ወይም ሌሎች ግለሰቦች በጉባዔው እንዲሳተፉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊጋበዙ ይችላሉ። ሆኖም ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸውም።

## 42. የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

ጉባዔው ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፡

1) የዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተኝነት፣ ተጠያቂነት እና ፍትህ አስተዳደር ረገድ በኢትዮጵያ በየትኛዉም ቦታ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ተወያይቶ መፍትሔ መስጠት፣
2) ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዚህ አዋጅ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ህጎች የተሰጠዉ ደንብ እና መመሪያ የማዉጣት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አሠራርን ለማሻሻል የሚረዱ መመሪያዎችና ውሳኔዎችን ማሳለፍ፣
3) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሃሣብ ማቅረብ፣
4) የዳኝነት ሥራ አካሄድን ለማቀላጠፍና ለማጠናከር የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን እና
5) ለጉባዔው ሥራ አፈፃፀም አስፈላጊውን ደንብ ማውጣት።

## 43. የጉባዔው አሠራር ሥነ-ሥርዓት

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል/ትሆናለች።
2) ጉባዔው የራሱን ፀሐፊ ይመድባል።
3) ጉባኤዉ ስራዉን ለማከናዎን የሚረዱ ኮሚቴወችን ያዋቅራል
4) ጉባኤዉ የራሱ ላይዘን ቢሮ እና ተጠሪዎች አስፈላጊ በሆኑ ፍርድ ቤቶችያቋቁማል፣
5) ጉባዔው የሥራ ባልሆኑ ቀናት በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ስብሰባም መጥራት ይችላል:
6) ከጉባዔው አባላት ሁለት ሶስተኛው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ይተላለፋል። ድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የጉባዔው ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖራቸዋል።

## ምእራፍ ዘጠኝ
## የፍርድ ቤት መር አስማሚነት እና የጉዳዮች አስተዳደር

## 44. የፍርድ ቤት መር አስማሚነት

1) በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሚቀርቡ የፍታብሄር ጉዳዮች ዉስጥ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ የሚወሰኑ ጉዳዮችበፍርድ ቤቶቹ በሚቋቋም የፍርድ ቤት መር አስማሚነት በኩል እንዲያልፉ ይደረጋል።
2) ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት መር አስማሚነት በኩል ጉዳያቸዉን በስምምነት ካልጨረሱ ይህንኑ የሚገልጽ በአስማሚዎቹ የተፈረመ ደብዳቤ ለፍርድ ቤት በማቅረብ የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል ይደረጋል።
3) የተስማሙ ከሆነ የስምምነቱ ሁኔታዎች በአስማሚዉ በግልጽ ተለይተዉ ከቀረቡ እና ተከራካሪዎቹ ከፈረሙበት ቡሃላ አስማሚዉ ይህን ሰነድ ለፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል።

ሰነዱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሰምምነቱ ለህግ እና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ቡሃላ እንዲጸድቅ ያደረጋል፡፡

4) የጸደቀዉ የስምምነት ሰነድ እንደማንኛዉም የፍርድ ቤት ዉሳኔ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
5) በአንደኛዉ ተከራካሪ ወገን ያለመቅረብ ምክንያት የመስማማት ሂደቱ ካልተሳካ አስማሚዉ ይህንኑ በመግለጽ ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡ መደበኛዉ የፍርድ ሂደትም ይቀጥላል፡፡
6) በፍርድ ቤት መር አስማሚነትም ይሁን በሌላ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ ግራ ቀኙ ከተስማሙ በደንቡ መሰረት ወጭዎች ተቀንሰዉ የከፈሉት የዳኝነት ክፍያ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡
7) የዚህን ድንጋጌ ለማስፈጸም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 45. ስለ አስማሚነት መርሆዎች

1) በፍርድ ቤት መር አስማሚነት የሚደረገዉ ማንኛዉም ሂደት በእኩልነት እና በባለጉዳዮቹን ሙሉ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡
2) በማስማማት ሂደቱ ተከራካሪ ወገኖች የሚሰጡት የእምነት ቃሎች ወይም ማንኛዉም ንግግሮች ለፍርድ ቤት በማስረጃነት አይቀርቡም፡፡ ለዚህም አስማሚዉ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
3) በፍርድ ቤት አስማሚነት በኩል የሚደረጉ ማናቸዉም የሃሳብ ልዉዉጦች ሚስጥራዊነት የተጠበቀ ነዉ፡፡

## 46. ስለ አስማሚዎች

1) የአስማሚነት ስልጠና ወስደዉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚያወጣዉን ምዘና ያለፉ ቢያንስ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸዉ እና ከአምስት አመት ያላነሰ ጊዜ በህግ ሙያ ያገለገሉ አስማሚ ሆነዉ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጸዉን ያሟሉ ባለሙያዎች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያዘጋጀዉ የአስማሚዎች ሮስተር መዝገብ ዉስጥ እንዲካተቱ ይደረጋሉ፡፡
3) እንደአስፈላጊነቱ ፍርድ ቤቱ ቋሚ የሆኑ ወይም በጊዜያዊነት ብቁ አስማሚዎችን ሊቀጥር ይችላል፡፡

## 47. ስለ ክፍያ

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 46 ንኡስ አንቀጽ (1) እና (2) የተገለጹ አስማሚዎች የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ የሚወሰን ለአስተዳደራዊ ጉዳይ እና አመታዊ ክፍያ ይከፍላሉ፡፡
2) አስማሚዎች በባለጉዳዮች ተመርጠዉ የማስማማት አገልግሎት ከሰጡ ተገቢዉ ክፍያ ይከፈላቸዋል፡፡
3) በማስማመቱ ሂደት ዉስጥ የሚያልፉ ባለጉዳዮች ለፍርድ ቤት መር አስማሚነት ተገቢዉን ክፍያ ይፈጽማሉ፡፡
4) ክፍያን በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ በጠቅላይ ፍርድ ይወጣል፡፡

## 48. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር

1) የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡላቸዉን ጉዳዮች የሚስተናገዱበት ወይም የሚጠናቀቁበትን የጊዜ ሰሌዳ ገደብ በማስቀመጥ የፍትህ አሰጣጥ ስርዓቱ የተሳለጠ እና ጥራቱ የሚረጋገጥበት የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ተግባራዊ ያደርጋሉ።
2) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጸዉን ለማስፈጸም ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

**49. <u>በቴክኖሎጅ የተደገፈ የመዝገብ አመራር ስርአት ስለመዘርጋት</u>**

1) የፌደራል ፍርድ ቤቶች በማንኛዉም የፍርድ ቤት ደረጃ የሚቀርቡ የፍታብሄር ወይም የወንጀል ጉዳይ ክርክሮች አዳዲስ የመረጃ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ዳጂታል ወይም አዉቶሜትድ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ስርዓት ሊዘረጉ ይችላሉ።
2) ተከራካሪ ወገኖች በተዘረጋዉ ስርኣት መሰረት ክርክሮቻቸዉን የማካሄድ ግዴታ አለባቸዉ።
3) ዝርዝሩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል።

## <u>ምእራፍ አስር</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**50. <u>የፍርድ ቤት ውሣኔዎችና ትዕዛዞች</u>**

1) በማንኛውም የፌዴራል ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በህግ እስካልተለወጠ ድረስ የፀና ሆኖ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸዉን ዉሳኔዎች ወይ ተእዛዞች በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ዉስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ። በማንኛዉም ክልል ዉስጥ የሚገኝ የመንግስት አካል፣ተቋም ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ማንኛዉም ሰው ውሳኔዎቹን ወይም ትእዛዞቹን የመፈጸም እና የማስፈጸም ግዴታ አለበት።

3) ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታ የማይወጣ ከሆነ በዚህ አዋጅና አግባብ ባለው ሌላ ህግ ተጠያቂ ይሆናል።

4) አንድን ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የክልል ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወይም የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተሞች ሥልጣናችን ነው ብለው የያዙት ወይም ሥልጣናችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ ስልጣኑን በሚመለከት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተገቢውን ትዕዛዝ ይሰጥበታል፡፡

**51. <u>ቅጣት</u>**

1) የፍርድ ቤት ወይም የዳኞችን በነጻነት መስራት የሚጋፋ ወይም በዳኞች ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ወይም ለማድረግ የሞከረ ማንኛው ሰዉ በሌላ ህግ ከፍ ያለ ቅጣት ከሌለ በቀር ከሦስት ወር እሥራት ባላነሰ ከሁለት አመት ባላበለጠ ጽኑ እስራት ይቀጣል።።
2) የፍርድ ቤትን ትእዛዝ ወይም ዉሳኔ የማይፈጽም ወይም ለመፈጸም መሰናክል የሚፈጥር ወይም ሲጠየቅ ለመፈጸም ተባባሪ የማይሆን ማንኛዉም ሰዉ በሌላ ህግ ከፍ ያለ ቅጣት ከሌለ በቀር ከሁለት አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ ገንዘብ ይቀጣል።

## 52. የዉጭ አማካሪ ምክር ስለማደራጀት

1) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከቀድሞ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ከፍተኛ ልምድ እና ብቃት ካላቸዉ የህግ ባለሙያወች፣ ከዩኒቨርስቲ ምሁራን የተዉጣጡ ያለክፍያ የሚሰሩ የዉጭ አማካሪዎችን በመምረጥ የዳኝነት ስርዓት የዉጭ አማካሪ ምክር ቤት ሊያደራጅ ይችላል።
2) የአማካሪ ምክር ቤቱ የፍርድ ቤቱን የዳኝነት ስርዓት ለማሻሻል የሚረዱ አስገዳጅ ያልሆነ ምክር ሃሳቦችን በማመንጨት እንዲሁም ሌሎች በፍርድ ቤቱ የሚሰጡትን ስራዎች በማከናወን የፍርድ ቤቱን አስተዳደር ያግዛል።
3) አማካሪ ምክር ቤቱ ስራዉን በሚያከናዉንበት ጊዜ የዳኝነት ነጻነትን እና የዳኝነት ስነምግባርን በማይጻረር መልኩ በጥብቅ ዲስፕሊን እና በከፍተኛ ሀላፊነት ስራቸዉን ማከናዎን ይጠበቅባቸዋል።
4) ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል።

## 53. ስለ ይግባኝ ማስፈቀጃ

1. ማንኛዉም በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ሰዉ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊጠይቅ የሚችለዉ ዉሳኔዉን ከሰጠዉ ፍርድ ቤት የይግባኝ ፈቃድ ሲያገኝ ነዉ።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ተግባራዊ የሚሆነዉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ ተለይተዉ በሚወሰኑ የፍታብሄር ጉዳዮች ላይ ብቻ ነዉ።

## 54. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን።

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀጥሎ የተጠቀሱትን በተመለከተ ደንብ እና መመሪያ ማውጣት ይችላል።

ሀ) ለሰበር የማይቀርቡ አነስተኛ መጠን ያላቸዉን ጉዳዮች

ለ) ስለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ገንዘብ አከፋፋል ፤

ሐ) በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ስለሚከፈል ቅጣት ፣ ስለወጪና ኪሣራ አከፋፈል እና

መ) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የችሎት አመራር ስነ ስርዓት ደንብ

2) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ ላይ የተጠቀሱ ጉዳዮችን በተመለከተ ደንብ እና መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

**55. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

1) ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በተጀመሩበት ፍርድ ቤት እና በነባሩ ህግ መስተናገዳቸዉ ይቀጥላል፡፡
2) በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 11 እስከ አንቀጽ 15 ድረስ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት አዋጁ ከጸደቀ **ከ6 ወር** ቡሃላ ይሆናል፡፡
3) የአስተዳደር ሠራቶኞች መተዳደሪያ ደንብ እስከሚወጣ ድረስ የሠራተኞች ቅጥር፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ እድገትና አስተዳደር የዚህን አዋጅ መርሆዎች ሳይቃረን ቀድሞ ሲሰራበት በነበረው ሕግ መሰረት ይቀጥላል፡፡

**56. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አዋጁን ለማሻሻል የወጡ ቁጥራቸው 138/1991፣ 254/1993፣ 321/1995 እና 454/1997 የሆኑ አዋጆች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

2) ይህን አዋጅ የሚቃረን ወይም በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ማናቸውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**57. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከ____ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ________ቀን 2012 ዓ.ም

**የተከበሩ ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ኘሬዚዳንት**